# ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ለኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት መስፋፋት ...

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ አንባቢያን፡፡ ባለፈው ሳምንት ዕትማችን ‹‹የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በለውጥ ጎዳና›› በሚል ርዕስ ከተቋሙ ዋናሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር አሸብር ባልቻ ጋር ያደረግነውን ቃለመጠይቅ አስነብበናችሁ ቀሪውን በክፍል ሁለት ዝግጅታችን ይዘን እንደምንመለስ ቀጠሮ ይዘን መለያየታችን ይታወሳል፡፡ ለዛሬ ደግሞ ‹‹ለኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት መስፋፋት ...›› በሚል ርዕስ ያጠናቀርነውን ጽሁፍ እንሆ ብለናል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ተልዕኮ የኃይል አቅርቦቱን በማሳደግ ኢኮኖሚው የሚፈልገውን ኃይል በአስተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ ነው፡፡ የኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ግንባታ፣ የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ፣ የጥገና እና የኦፕሬሽን እንዲሁም የጅምላ ኃይል ግዢና ሽያጭ ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መሰጠቱን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ኢንጂነር አሸብር መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

እንደ ኢንጂነር አሸብር ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ለሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆን በተለይም የማከፋፈያ ጣቢያዎችና የማስተላለፊያ መስመሮች መስፋፋት አለባቸው፡፡ ተቋሙ የዜጎችን የኃይል ፍላጎት ጥያቄ ለመመለስ እንዲሁም ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ጉልህ ድርሻ አስተማማኝ ለማድረግ ቀን ከሌት እየታተረ ይገኛል፡፡ ከትንንሽ እስከ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች ኃይል ሳይቆራረጥ ተደራሽ ማድረግ መቻሉና ከዚህ የሚተርፈውን ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን ማሳደጉ የስኬቱ አንድ ማሳያ ነው፡፡

አሁን ያለው የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ተበታትኖ ለሚኖረው 120 ሚሊዮን ለሚገመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይል ለማዳረስ በቂ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ ሙሉ ለሙሉ



ኢንጂነር አሸብር ባልቻ

ሕዝቡን ተጠቃሚ ለማድረግ አሁን ያለውን የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት አቅም በእጥፍ ማሳደግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ይህንን ለመለወጥ ተቋሙ አዳዲስ የመሠረተ ልማት ግንባታ እና የማስፋፊያ ሥራዎች እያከናወነ እንደሚገኝ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ገልፀዋል፡፡ ኢትዮጵያ ካላት ቆዳ ስፋትና እያደገ ከሚሄደው የሕዝብ ቁጥር አንጻር የኤሌክትሪክ ኃይልን ተደራሽ ለማድረግ ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅባት አስምረውበታል፡፡

በኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች እንዲሁም ማሰራጫ መስመሮች ክልሎች የሚያነሱት የፍትሃዊነት ጥያቄ እንዳለ የተናገሩት ኢንጂነር አሸብር፤ ጥያቄውን ለመመለስ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመምከር ከዚህ በኋላ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች የሁሉንም ክልሎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መንገድ መገንባት እንዳለባቸው ስምምነት ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል፡፡

ተቋሙ የኃይል ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር መሠረተ ልማቶችን እየገነባ ተጨባጭ ለውጦችን ማስመዝገብ ቢችልም ጉዞውን የሚያደናቅፉና ግስጋሴውን ወደ ኋላ የሚስቡት ፈተናዎች እያጋጠሙት እንዳሉም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል፡፡ ዋና ዋና የሚባሉት ተግዳሮቶች ከካሳ ክፍያ፣ ከስርቆት፣ ከጸጥታ ችግር፣ ከግብዓት አቅርቦት እጥረት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ በተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ድጋፍ ከሚመለከታቸው የክልል የመስተዳድርና የጸጥታ አካላት ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር እንደተቻለና ለማህበረሰቡም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች እንደተሰጡ አስረድተዋል፡፡ በተሠራው ሥራ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ውጤት እንደታየ ገልጸው በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ግን አሁንም ችግሩ እንደሚስተዋል ጠቅሰዋል፡፡ የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠልና ቀደም ሲል የተገነቡትን ለመጠገን አዳጋች ሁኔታዎች እንደተፈጠሩ ገልጸዋል፡፡ ለአብነትም ምዕራብ ወለጋን ጠቅሰዋል፡፡

በአብዛኛው ቦታ የሚጠየቀው የካሳ ክፍያ መጠን ከፍተኛ መሆን ለሥራዎች መጓተት ምክንያት ከመሆን ባለፈ ክፍያው እስከሚፈጸም ድረስ ፕሮጀክቶች የማይጀመሩበት ሁኔታ አለ ብለዋል፡፡ በኤሌክትሪክ የብረት ማማዎች ላይ የሚፈጸመው ስርቆትም እንዲሁ የተቋሙን ኢኮኖሚ በሁለት መንገድ የሚጎዳው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያው የተሰረቀውን ብረት ለመተካት የሚወጣው ከፍተኛ ወጪ ሲሆን ሌላው በአገልግሎት በመቋረጥ ምክንያት ተቋሙ የሚያጣው ገቢ ነው፡፡ ከማማዎች ላይ የሚሰረቁ ብረቶች መዳረሻቸው የብረት አቅላጭ ፋብሪካዎች እንደሆኑ የተናገሩት ኢንጂነር አሸብር፤ በጉዳዩ ዙሪያ ከሚመለከታቸው የፋብሪካ ባለሀብቶች ጋር ውይይት ይደረጋል ብለዋል፡፡ እነዚህን ችግሮች መፍታት ካልተቻለ ግን የኤሌክትሪክ መሠረት ልማትን በማስፋፋት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ኃይልን ተደራሽ ለማድረግ የተጀመረው እንቅስቃሴ እንደሚደናቀፍ ስጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር አሸብር ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋናው የገቢ ምንጩ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የፋይበር ኦፕቲክስ መስመሮችን ለኢትዮ ቴሌኮም፣ ለሳፋሪኮም እና ለሌሎች ተቋማት በማከራየት ተጨማሪ ገቢ እያገኘ ነው፡፡ በሀገሪቱ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ጥቅም ላይ መዋል በመጀመራቸው ቻርጅ ማድረጊያ አማራጮችን በመገንባት ተቋሙ ገቢውን ለማሳደግ የሚችልበት ተጨማሪ ዕድል ተፈጥሮለታል፡፡ በዚህ ዙሪያም ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመሥራት እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

ተቋሙ የኤክስፖርት አቅሙን በማሳደግ የገቢ ምንጩን ለማሳደግ አልሞ እየሠራ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከሚያመርተው ኃይል አስር በመቶ የሚሆነውን ለጂቡቲ፣ ለሱዳን እና ኬንያ ኤክስፖርት አድርጎ የገቢውን ሰላሳ በመቶ እያገኘ መሆኑን ኢንጂነር አሸብር ተናግረዋል፡፡ ሶማሌ ላንድ ፣ ደቡብ ሱዳን እና ታንዛኒያን የመሳሰሉ ጎረቤት ሀገራትም ተመሳሳይ ፍላጎት እንዳላቸውና የተወሰኑት ስምምነት እንዳደረጉ ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የኃይል ማዕከል በመሆን እስከ ዛምቢያና ደቡብ አፍሪካ የሚዘልቅ አገልግሎት ለመስጠት አስባ እየሠራች ነው ብለዋል፡፡

ተቋሙ ከፍተኛ ኃይል በማምረትና መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት መላውን የአገሪቱን ሕዝብ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም ኃይል በመሸጥ በሚገኘው ገቢ መሠረተልማቱን ለማስፋፋት የሚያደርገውን ጥረት የሚያደናቅፉ እኩይ ተግባራትን መታገል የሁሉም ኃላፊነት በመሆኑ ኅብረተሰቡ፣ ሚዲያው፣ የጸጥታ ኃይሉ እና በየደረጃው ያለው አመራር እገዛ እንዲያደርግ ኢንጂነር አሸብር ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል